# የዋስትና መብት በኢትዮጵያ ህግ ማዕቀፍ በትንሹ

በጌታዬ አባይ ደረጄ*

## መግቢያ

የዋስትና መብት መሰረታዊ ከሆኑት የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶችን በተመለከተ ዓለም ዐቀፍ ሰነዶች እንዲሁም ስምምነቶች እውቅና የሰጡት መብት ነው፡፡ ለአለማቀፉ ህጎጋት መሰረት የሆነው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀፅ 9(3) በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ዋስትና ተነፍገው ጉዳያቸውን በእስር ሆነው የሚከታተሉበት ሁኔታ ጠቅላላ መርህ ሲሆን እንደማይገባ ተደንግጓል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያጠናው ጥናትም እንደሚያሳየው ዋስትና ተነፍገው በዕስር ቤት ሆነው ጉዳያቸውን የሚከታተሉ ሰዎች የዋስትና መብት ተከብሮላቸው ከዕስር ውጭ ሁነው ከሚከራከሩ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር በፍርድ ነፃ የመባል ዕድላቸው እጅግ አናሳ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህም የሚያሳየን የዋስትና መብት አለመከበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሌሎች መብቶች እንዲጣሱ በር የሚከፍት መሆኑ ነው፡፡ የዋስትና መብት ከበርካታ መሰረታዊ መብቶች ጋር የሚገናኝ ሲሆን ከእነዚህ መካከል በፍርድ ሂደት ወንጀለኝነት እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሁኖ የመገመት መብት፣የነፃነት መብት፣ካልተገባ አያያዝ የመጠበቅ መብት እና የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከህገ-መንግስቱ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የዋስትና መብት መርህ ሲሆን በዋስ አለመፈታት ደግሞ ልዩ ሁኔታ መሆኑ ነው፡፡ ዋስትና መከልከል ሁሌም ስልጣኑ የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ፅሁፍ ዋስትና ምንድን ነው፤ የዋስትና አይነቶች፤ዋስትናን ለመፍቀድና ለመከልከል ቅድመ ሁኔታዎች፤ዋስትና መቼ ይቀራል፤ የዋስትና መብት አለመከበር የሚያስከትላቸው ጉዳቶች፤የዋስትና መብት መከበር የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ፖሊስ የዋስተና መብቱ በተከበረለት ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላል ወይ? በአካል ነፃ መውጣት መብት የሚሉትን ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ የተወሰዱበትን ምንጮችንም በግርጌ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ አስተያየትና ጥያቄ ካለዎት ከታች በተቀመጠው አድራሻ ላይ ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡

………………

*የመቄት ወረዳ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሂደት አስተባባሪ ዳኛ

አድራሻ፡ getayeebayi@gmail.com or

: https://twitter.com/gech69826226?s=35

➢ ፅሁፉን በኮንፒውተር የፃፈልኝን አቶ ጎበዛየሁ ደጀንን እጅግ አድረጌ አመሰግናለሁ፡፡

# ***የዋስትና መብት ህጉና አተገባበሩ***

ዋስትና ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ ትርጉሙ በግልፅ በህጎቻችን ተቀምጦ አናገኘውም። ከህጎቻችን ይዘት እና መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው ዋስትና ማለት በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ወይም የተከሰሰ ሰው የተጠረጠረበት ወንጀል ምርመራ እስኪጠናቀቅ ወይም ክሱ በፍ/ቤት ታይቶ ውሳኔ እስኪያገኝ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሚፈለግበት ጊዜና ቦታ ለመቅረብ ግዴታ ገብቶ ወይም ግዴታውን የሚወጣለት ቃል ጠርቶ ከእስር የሚለቀቅበት ስርዓት ነው፡፡[1] መዝገበ ቃላዊ ፍቹን በተመለከተ‹‹bail is the right to be released from custody before the case is concluded, or sentence is passed, assuming there is no risky of absconding or committing offence while on bail.[2] ይህም ከላይ ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የዋስትና መብት ማለት ተጠርጣው የማይሰወር፣ተጨማሪ ወንጀል የማይፈፅም ከሆነ ከውሳኔ በፊት ተጠርጣሪው ከእስር የሚለቀቅበት ነው እንደማለት ነው፡፡[3] ዊክፒዲያም ‹‹Bail is the conditional release of defendant with the promise to appear in the court whene required›› ይለዋል፡፡ዋስትና ማለት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ፍርድ ቤት ሲፈለግ ለመቅረብ ግዴታ ገብቶ በጊዜዊነት የሚለቀቂበት እንደማለት ነው፡፡[4] በህግ እዉቁ መፅሐፍ Blacks' Law Dictionary እንዲህ በማለት ይገለፀዋል፡፡‹‹Bail is asecurity requried by the court or police for the realese of an accused person or aprisoner who must appear in court or police station in afuture time.[5] ትርጉሙም ከላይ ከተገለፁት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለቀጣይ ቀጠሮ ተጠርጣሪው ለመቅረብ የሚገባው ግዴታ ነው፡፡ታዋቂው Contemporary Restatment of American LAW, Corpus Juris Secondum ዋስትና የሚለውን ቃል በግስ እና በስም እንደሚከተለው ያብራራዋል፡፡ ‹‹The bail as **averb** means to deliver an arrested person to his sureties on their giving security for his apearace, at the time and place designated, to submit to the jurisdiction and judgment of the court.ሲለው
As **anoun,** the person in whose custody the defendant is placed whene released from jail, and who acts as asecurity for defendant's later apperance in court.[6] ከላይ ያየናቸው ትርጉሞች ዋስትና ማለት አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ወይም የተጠረጠረ ሰው የገንዘብ፣የሰው፣ወይም የንብረት ዋስ በማስያዝ ለጊዜው ከእስር የሚፈታበት ነው፡፡[7] ይህም መብት ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ሳይሆን ገደቦች ያሉበት መብት ነው፡፡ ‹‹bail is right not privilege የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ Mchome ተባለ ሰው ስለ ዋስትና ተከታዩን ፅፏል፡፡ Bail is an agreemnt between the accused /his

---

[1] ዑስማን መሃመድ ሰይድ-ህገ መንግስታዊ የዋስትና መብት በመተርጎም ስለታየው ችግር ገፅ የሌለው

[2] https://www.lexiisnexis.co-uk/legal/grossary/bail/ የተወሰደበት ቀን May23/2023.

[3] ትርጉሙ የተወሰደበት ካልተገለፀ በስተቀር የራሴ ነው፡፡

[4] https://en.m.wikipedia.org/wiki/main_page የተወሰደበት ቀን May 23,2023

[5] Blacks' Law Dictionary 9th ed.page-135

[6] Kalali Kiros,The bail justice in Ethiopia challenges of its administration.page 6 & C.J.S.Bailment p.9

[7] Content://com.mi.android.global file expiorer.myprovider/external_files/Dowload/%FO%Gf%93%8c%20%1%20Facebook.

surities if any/ and the court that the accused will pay acertain sum of money fixed by the court,spesfied date.[8] በግርድፉ ዋስትና ማለት በተጠርጣሪውና ፍ/ቤት መካከል ያለ ስምምነት ሲሆን ተጠርጣሪው ለተወሰኑ ቀናት ገንዘብ በማስያዝ የሚቆይበት ነው፡፡ Hampton የተባለ ሊቅ ደግሞ ተከታዩን ብሏል፡፡ ‹‹Bail is temporary release of an accused after entering into an agremeent between an accused person in the court or police for releasing him to the custody of the surity[9]. Peter የተባለ ሰውም ‹‹bail can be defined as an agremeent entered into between an accused person and the court or police for releasing from custody and entrusting him to the custody of the surety upon certain conditions pending the finalization of court proceedings.ብሏል፡፡[10] ሌላም ሊቅ ተከታዩን ብሏል፡፡bail is the right given to the suspect or the accused person to be released or befree from custody while waiting for further investigations and other criminal procedures to take place or to continue taking place.[11] ይህም ተጨማሪ ምርመራ በሚኖርበት ጊዜ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ከእስር የሚለቀቅበት መብት መሆኑን ነው የምንረዳው፡፡

Ingman የተባለ ሊቅም ‹‹Bail as are release from custody pending criminal trial,of defendant on balancing of competing interests and on the promise that aspecified predetrmined amount of money will be paid if he absconds›› በማለት ያብራራዋል፡፡[12] የዋስትና ሥርዓት ሌላው ገፅታ መብትን ማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን በመብት ተጠቃሚው በኩል ግዴታን መግባት የሚጠይቅ ሥርዓት መሆኑ ነው፡፡[13] ይህ መብት በህገ-መንግስትም ሆነ የህገ መንግስቱ የበታች የሆኑ በርካታ ህጎች የታፈረ እና የተከበረ መሰረታዊ ከሆነው የሰው ልጅ የመዘዋወር ነፃነትና ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያለው ሰብዓዊ መብት ነው፡፡[14] በአጠቃላይ ከህጎቻችን ይዘት እና መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው ዋስትና ማለት በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በቁጥጥር ስር የመሆን ግዳታ ግልባጭ መብት ነው ማለት ይቻላል፡፡[15] በተለይም በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ሰው ጉዳዩ በማስረጃ ተረጋግጦ ጥፋተኝነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ የገንዘብ ወይም በቂ የሰው ዋስ በማቅረብ ከእስር ነፃ ሆኖ የፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጠሮ ቀን እየቀረበ የሚከታተልበት የህግ ሥርዓት ነው፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስም ዋስትና መሰረታዊ መብት ነው፡፡[16] ይህ መብት በህገ መንግስቱም የሰብዓዊ መብት አካል ነው፡፡ አለም አቀፉ የሲቭል እና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግስት መርማሪ አካላት ያለበቂ ምክንያት እና ህገጋዊ ስርዓት የአንድን ሰው ነፃነት መብት እንዳይጥሱ ዋስትና እና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡[17] የተያዘው ሰው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(3) እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ ህግ አንቀፅ 29(1) መሰረት በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት የመቅረብ መብት እንዳለው የተደነገገት ይህንኑ ሰብዓዊ መብት ለማረጋገጥ ነው፡፡[18] ፍ/ቤቱም በተገለፀወው ጊዜ ተጠርጣሪው ሲቀርብለት በወ/መ/ሥ/ሥ ህግ

---

8 Mchom,S.E-Criminal procedure,OPEN Universty,Manual p-95

9 G.Hampton - criminal procedure.3rdedition London.

10 Peter.C.M. Human rights selected cases and materials.p-527

11 Asherry Magalla,the law relating to bail;why is it difficult to grant bail to some of the offences

12 Kalali Kros, The bail justice in Ethiopia challenges of its administration.page 6

13 ዑስማን መሃመድ ሰይድ-ህገ መንግስታዊ የዋስትና መብት በመተርጎም ስለታየው ችግር ገፅ የሌለው

14 አማራ ክልል የፍትህ ባለሙያወች ማሠልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢኒስቲትውት የህግ መፅሄት -ቅፅ 5 -ገፅ 75

15 Ibid page- 77

16 https://www.abyssinianlaw.com/blog/2015-08-24-08-37-36 የተወሰደበት ቀን May03/2023

17 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀፅ-19(6)

18 https://www.abyssinianlaw.com/blog/2015-08-24-08-37-36 የተወሰደበት ቀን May03/2023

አንፅ 59 መሰረት በማረፊያ ቤት እንዲቆይ/Remand/ ወይም በዋስትና እንዲለቀቀ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ ይህም በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳዩ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ታይቶ ጥፋተኛ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ከወንጀል ነፃ እንደሆነ የመቀጠር መብት ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ መብት ዕውቅና ሊያገኝ የቻለው ንፁህ ግለሰቦች በወንጀል በመጠርጠራቸው ወይም በመከሰሳቸው ብቻ ሊደርስባቸው የሚችለውን የመብት ጥሰት ለመግታት የታሰበ ነው፡፡[19] ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተያዘ ሰው በመሰረቱ የተያዘበት/የተጠረጠረበት/ ወንጀል በማስረጃ ከተረጋገጠበት ሊፈረድበት ማስረጃ ከሌለ ግን የሚለቀቅ ቢሆንም መርማሪ ፖሊስ ወይም ዓ.ህግ ጉዳዩን እስኪያጣሩ እና ለፍ/ቤት እስኪያቀርቡ ድረስ ታሳሪው በጥፋተኝነት የማይቀጣበት ወይም በፍፁም የማይለቀቅበት ሁኔታ አለ፡ ይህም በዋስትና የመለቀቅ መብት ሲሆን የሰው ልጅ እንደፈለገ ለመዘዋወር ሁለት እግሮች የተሰጡት፤በአንድ ቦታ ተወስኖ እንዳይቀመጥ ሰዋዊ ተፈጥሮ ነፃ አድርጎ የፈጠረው ይህንን ተፈጥሮውንም አብዝቶ የሚወድ ነፃ ፍጡር በመሆኑ ነው፡፡[20] ይህ ነፃ የሆነ ሰው በህግ ከመዘዋወር ሊከለከል፤በአንድ የተወሰነ ሥፍራ ተወስኖ ሊቀመጥ የሚችለው ለጠቅላላው የህዝብ ጥቅም ሲባል የጠቅላላውን ህዝበ ጥቅም ከአደጋ ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ ምን አልባት የተጠርጣሪው የዋስትና መብት ማክበር ይህንን የጠቅላላውን ህዝብ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ለመታደግ ሲባል ብቻ ነው፡፡ መንግስት የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ የማስከበር ሀላፊነት አለበት፡፡ይህንን ሀላፊነት ሲወጣ የወንጀል ተግባር ፈፅመዋል በማለት በሚይዛቸው ሰዎች ላይ ህግ ለማስከበር የሚፈፅማቸው ተግባር ሁለት ተፋላሚ የሆኑ ጠቅሞችን የማስታረቅ እና ፀጥታ ለማስጠበቅ ሲባል በከባድ የወንጀል ተግባር የተጠረጠሩ ሰዎችን በፍርድ አደባባይ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ ከፍርድ በፊት ማሰሩ ተገቢ ሲሆን በሌላ በኩል ተጠርጣሪ ሆነው የታሰሩ ሰዎች ንፁህ ሰዎች የሚሆኑበት ዕድል ሰፊ ስለሆነ ከፍርድ በፊት እንዳይታሰሩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቃል፡፡[21] አሜሪካኖቹ ‹‹An arrestee's right to pre-conviction release is related with the presumption of innocence››ነው የሚሉት፡፡ የአሚሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የዋስትና መብትና ንፁህ ሆኖ የመቆጠር መብት ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ለመግለፅ ‹‹ከፍረድ በፊት የዋስትና መብት ካልተከበረ በዘመናት ትግል የመጣው የንፁህ ሆኖ የመቆጠር መብት ትርጉም ያጣል›› ብሏል፡፡[22]

# የዋስትና መብት አመጣጥ ታሪካዊ ዳራ

የዋስትን መብት በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በተጠረጠረበት ወንጀል ጉዳዩ እስኪጠናቀቅ ወይም ክሱ በፍ/ቤት ታይቶ ውሳኔ እስኪያገኝ በሚፈለግበት ጊዜ እና ቦታ ለመቅረብ ግዴታ ገብቶ ወይም ግዴታውን የሚወጣለት ዋስ ጠርቶ ከእስር የሚለቀቅበት ስርዓት መሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡ የወንጀል ተግባር ፈፅሟል ተብሎ በጥርጣሬ የተያዘን ሰው ወደ ፍርድ አደባባይ አቅርቦ በወንጀል ህግና ሥነ-ሥርዓት ህጉ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ

---

[19] https://www.abyssinianlaw.com/blog/2015-08-24-08-37-36 የተወሰደበት ቀን May03/2023
[20] ሙሉጌታ በላይ-መስከረም 18/1015 በ abyssinianlaw blog ከለቀቀው የተወሰደ የተወሰደበት ቀን ግንቦት 03/2023 ነው፡፡
[21] ዑስማን መሃመድ ሰይድ-ህገ መንግስታዊ የዋስትና መብት በመተርጎም ስለታየው ችግር ገፅ የሌለው
[22] Wondossen Demissie-The right to bail in Ethiopia: Respective role of the court and the legislature.P 3. ‹‹**unless this right to bail before trail is preseved, the presumtion of innocence, secured only after centuries of struggle, whoud\ld lose its meaning››**

በጊዜ ቀጠሮ በማረፊያ ቤት ከማቆት ይልቅ የዋስ መብቱን ጠብቆ መልቀቅ ይሻላል የሚለው መሰረተ ሀሳብ በሁሉም ሀገሮች ተቀባይነት አግኝቶ ተግባር ላይ ከዋለ አያሌ ዘመናት አልፈዋል፡፡ የተጠርጣሪዎችን የዋስ መብት በመፍቀድ መልቀቅ የተጀመረበትን ዘመን በግልፅ ለመናገር ባይቻልም የዋስ መብት መነሻው በጥንት ዘመን የእንግሊዝ እና የሮማን ህግ እንደ ነበር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡[23] ሆኖም በጥንት ዘመን ለምን አገልግሎት ይውል እንደነበር ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ አገልግሎቱ ማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም የፅንሰ ሃሳቡ /notion/ ታሪክ መነሻው ሮም ነው፡፡[24] በሮማን ህግ ዋስትና የተለመደው ተከሳሽ በቀጠሮ ቀን እንዲገኝ ለማድረግ ሲሆን አንግሎ አሜሪካን በኩል ዋስትና የሚለው ጉዳይ የተጀመረው በሸሪፎች /sheriffs/ተጠርጣሪዎችን በቀጠሯቸው ቀን እንዲቀርቡ የዘየዱት ዘዴ እንደሆነ ይገመታል፡፡[25] የወንጀል ተግባር የፈፀሙ ሰዎችን አስረው የመጠበቅ ስልጣን የነበራቸው ሸሪፎች ከዚህ ከፍተኛ ወጭ ሀላፊነት ለመዳን የፈጠሩት ነው ይባላል፡፡ በወቅቱ ዳኞች ከአንድ ሀገር ወደ ሌላው አገር እየተዘዋወሩ ዳኝነት ይሰጡ ስለነበር ተጠርጣሪዎች ተራ ደርሷቸው ጉዳያቸው እስኪሰማ ድረስ ብዙ ጊዜ ስለሚወስድና እስር ቤቶች ለጤና ተስማሚ ስላልነበሩ ብዙ እስረኞች ጉዳያቸው ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት በእስር ላይ እንዳሉ ይሞቱ ነበር፡፡[26] ይህ አይነቱ አሳዛኝ ሁኔታ ሸሪፎች እስረኞችን በራሳቸው ዋስትና ወይም ፍ/ቤት ሊያቀርባቸው በሚችል በሌላ ሰው ዋስትና ከእስር ይለቋቸው ነበር፡፡ ይህ እስረኞችን በዋስ የመልቀቅ ተግባር ይፈፅም የነበረው ለሸሪፎች በህግ እና በመመሪያ በተሰጠ ሥልጣን ሳይሆን በራሳቸው ሀላነት ከእስረኞች ጋር በሚፈፅሙት ስምምነት ብቻ ነበር፡፡ ይህ ሂደትም ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ በኋላ ህግ ሆኖ መጣ፡፡ አሁን ያለው ዋስትና የመጣውም በዚህኛው መንገድ ነው፡፡[27] በሂደት ተጠርጣሪዎችን በዋስ የመልቀቅ እና የመያዝ ሥልጣን የፍ/ቤት ብቻ እየሆነ መጣ፡፡ ወደ ሀገራችንም ስንመጣ በባህላዊ መንገድ የወንጀል ሥነ ስርዓት እና የዋስትና ፅንሰ ሀሳብ በተግባር ሲሰራበት መኖሩን የሚያረጋግጡ ፅሁፎችን ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ ህግ ከመታወጁ በፊት የዋስትና ተቋማት መኖራቸው ግን አይካድም፡፡[28] ይህም ለቀጣይ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማድረጊያ መንገድ ነበር፡፡ በጊዜው እስር ቤቶች ባለመኖራቸው ሁለት ዓይነት ዋስትና ነበሩ፡፡ እነዚህም ቁራኛ (koragha) እና ዋስ (sureties) ነበሩ፡፡[29] በዘመናዊ የህግ አስተሳሰብ መሰረት በዋስ ለመለቀቅ ከሚያበቁ ምክኒያቶች መካከል ጎልቶ የሚታየው ‹‹ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍ/ቤት ገና የጥፋተኝነት ውሳኔ ሣይሰጥበት ሊቀጣ አይገባውም›› የሚለው ነው፡፡ በአስተዋይነት የተሞላው ይህ የዘመናዊ ህግ አስተሳሰብ መሰረት ወንጀል ሰርቷል በመባል የተከሰሰ ሰው በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት በህጋዊ መንገድ የተሰበሰቡ ማስረጃዎችን ሰምቶ የጥፋትኝነት ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ንፁህ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ እንዲህ ያለው ሰው ጥፋተኛ መሆኑ ገና ሳይረጋገጥ በእስር ቤት እንዲቆይ ማድረግ ንፁህን ሰው ያለጥፋቱ እንደመቅጣት ስለሚቆጠር በዋስ መልቀቅ የተሻለ አሰራር ሆኖ ተገቷል፡፡[30] በሌላም በኩል ክርክርን በአጭር ጊዜ ለመጨረስ የሚያስችል ሥርዓት/speedy trial/ መኖሩን እርግጠኛ ባልተሆነበት ሁኔታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሟል በሚል ክስ ስለቀረበበት ወይም ሊቀርብበት ስለሚችል ብቻ ዋስትና መከልከል ትክክል አይደለም የሚሉ አሉ፡፡[31] የዋስትና መብት ለጠቅላላው ህዝብ ጥቅም

---

23 Wondossn Demissie Kassa, criminal procedure-p 207
24 Timothy R. Schnacke-The history of bail and pretrial release
25 Wondossn Demissie Kassa, criminal procedure-p 207
26 ሙሐመድ አህመድ -በአፋር ብ/ክ/መንግስት ዳኞች ከተሰጠው ሥልጣና የተወሰደ
27 Wondossn Demissie Kassa, criminal procedure-p 207
28 Ibid page 209
29 Kalali Kiros, The bail justice in Ethiopia challenges of its administration, Addis Ababa Universty, school of law, 2011 page-17
30 https://www.abyssinianlaw.com/blog/2015-08-24-08-37-36 የተወሰደበት 22 Jun,2023
31 https://www.abyssinianlaw.com/blog/20/ የተወሰደበት 22 Jun,2023

ሲባል ሊገደብ ቢችልም ጉዳዩን በአጭር ጊዜ አይቶ ለመወሰን የሚያስችል የሰው ሀይል፤አሰራር እና ሥርዓት ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አንድን ሰው አስሮ ማቆየት ተገቢ አይደለም ከሚል ሀሳብ የመነጨ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በአጭር ጊዜ ፍትህን የማግኘት መብትና ካላስፈላጊ የፍትህ መዘግየት መጠበቅ መብት አለው፡፡[32] የዘገየ ፍትህ እልዳልተሰጠ ይቆጠራል/justice delay justice deny/ እንደሚባለው የሰው ልጅ ጉዳዩን በአጭር ጊዜ ውስጥ የማወቅ ተፈጥሯዊ ፍላጎት ያለው በመሆኑ የካሳ ስርዓት ባላዘጋጀች እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሀገር ውስጥ ለረጅም ጊዜ በእስራት መቆየት ተጠርጠሪዎችን በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ ይህንን ካሳ የሌለውን ጉዳት/irremediable damage/ ለማስወገድ የተጠርጣሪውን ነፃነት ለማስጠበቅ የዋስትና መብትን በአግባቡ መተግበር አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡[33] በካሳ መልክ ማካካስ ቢቻልም እንኳ ይህንን ማድረግ የሚያስችል የህግ ሥርዓት ባለመኖሩ የዋስትና መብትን ተግባራዊ ማድረግ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡

# የዋስትና የስረ- ነገር ሥልጣን

የዋስትና የስረ ነገር ሥልጣን ጉዳዩ በማንኛውም ፍርድ ቤት ይቀርባሉ የሚለው በመርህ ደረጃ በአቅራቢያ በሚገኝ ፍ/ቤት የሚታይ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የወ/መ/ስ/ስ ህግ አንቀፅ 64 ንዑስ ቁጥር 3 በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ስለሚል ወሰኑ በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ ለማህበራዊ ፍ/ቤት መቅረብ ይችላል ወይ የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ምክንያቱም በህግ የተቋቋመ ፍ/ቤቶች ናቸውና፡፡[34] የፌደራል ጉዳይ ውክልና ስልጣን የሌለው የወረዳ ፍ/ቤት ሊያየው ይችላል ወይ የሚለውም ሌላው አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡

# የዋስትና አይነቶች

ከሚፈቅዱት አካላት ጋር ተያይዞ ዋስትና በሁለት ልንመድበው እንችላለን፡፡

1. **የፖሊስ ዋስትና፡**-ወንጀሉ ፅኑ እስራት የማያስቀጣ ከሆነ እና ተጠርጣሪው ወንጀሉን ለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 28 መሰረት ፖሊስ የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቀው ይችላል፡፡
2. **ፍ/ቤት ዋስትና፡**-በወንጀል ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 59/1 መሰረት ፖሊስ በወንጀል ጠርጥሮ በመያዝ ለፍ/ቤት ያቀረበውን ተጠርጣሪ በዋስትና ወረቀት ሊለቀው ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለው፣ምርመራ እየተካሄደበት ከሆነ መለቀቁ በማስረጃ ማሰለባሰቡ ሒደት ላይ እንቅፋት የማይፈጥር፣ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ የሚቀርብ መሆኑን፣መለቀቁ ለህዝብ ፀጥታና ሰላም አስጊ አለመሆኑንና ሌላ ወንጀል የማይፈጽም መሆኑን በማገናዘብ ነው፡፡[35]

በሌላም በኩል በሚያዘው ዋስትና በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡

1. በገንዘብ የሚፈቀድ ዋስትና/Monetary Bail/ በገንዘብ ዋስ የሚለቀቅ
2. በገንዘብ ያልሆነ ዋስትና/Non-Monetary Bail/ ለምሳሌ የሰው ዋስ፤የስራ ዋስ …ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ዋስትና በሶስት የሚከፈል ሲሆን፡-

ሀ. Personal recognizance- በራሱ ተጠርጣጥው በመፈረም የሚወጣበት ነው መንገድ ሲሆን የራስ ዋስትና ይባላል፡፡

ለ. Unsecured appearance bond የስራ ዋስ

---

[32] ibid

[33] Simeneh Kirose Assefa, Criminal Procedure law,principles, Rules and Practices page 234

[34] ሰለሞን ጎራው አዳነ-የወንጀል ስ/ስ/ህግ ጠቅላላ መግቢያው-የቅድመ ክስ ሒደቱ-ገፅ 40

[35] ሰለሞን ጎራው አዳነ-የወንጀል ስ/ስ/ህግ ጠቅላላ መግቢያው-የቅድመ ክስ ሒደቱ-ገፅ 42

ሐ. Third party Release የሶስተኛ ወገን ዋስ ማለት ነው። ሰዎችን በተያዥነት እንዲያቀርብ ማድረግ ነው።
መ. ለተወሰነ የመንግስት አካል በቋሚነት ሪፖረት እንዲያቀርብ በማድረግ/Supervised release/ ሌላኛው የዋስትና መንገድ ነው።

በገንዘብ የሚፈቀድ ዋስትና እንደገና በሶስት የሚከፈል ሲሆን
ሀ. Cash Bail ተጠርጣሪው በካሽ ገንዘቡን ከፍሎ ከእስር የሚለቀቀበት ሁኔታ ነው።
ለ. Corporate Surety Bail ለምሳሌ ፈቃድን በመስጠት ከእስር የሚለቀቀበት ሲሆን
ሐ. Cash by Personal Surety[36] ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ።
ከወንጀሎቹ አንፃርም በሁለት ልንከፍለው እንችላለን።

1. **ዋስትና የማያስከለክሉ ወንጀሎች**/Bailable Offenses/ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በወንጀል ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 63 መሰረት የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣት ወይም 15 ዓመት ወይም በላይ ያልሆነ ፅኑ እስራትና ተጎጅው የማይሞት ከሆነ ፍ/ቤቱ በዋስ ወረቀት አስፈርሞ ሊለቀው ይችላል። የተጠቀሱት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው የሚሉ አሉ።በሌላም በኩል መሟላት የለባቸውም የሚሉ አሉ። መሟላታቸው ለመፍቀድ እንጅ ለመከልከል አንዱ መስፈርት ብቻ መገኘቱ በቂ ነው።[37]
2. **ዋስትና የሚያስከለክሉ ወንጀሎች**/Non-Bailable Offenses/ የወንጀል ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 63 ስር የተዘረዘሩት መስፈርቶች አንዱ ተሟልቶ መገኘት፣የወንጀል ህግ አንቀፅ 543/3/፣የጸረ-ሙስና አዋጅ ቁጥር883/2007[38]፣ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 348/96፣የቀድሞው የሽብር አዋጅ ፤ዋስትና ከሚያስከለክሉ ወንጀሎች ተጠቃሾች ናቸው።ሌላው ዋስትና የሚያስከለክለው የወንጀለኛ መወሰኛ ስ/ስ/ህግ ቁጥር አንቀፅ 67 ስር የተዘረዘሩት መስፈርቶች ፍ/ቤቱ ካመነበት ሊያስከለክሉ የሚችሉ ናቸው። አዲሱ የወንጀል ህግ መቶ የሚደርሱ የተለያዩ ወንጀሎች ዋስትና ያስከለክላሉ። ይህም ከጠቅላላ የወንጀል ህጉ 25% የሚሆን ነው።[39] በወንጀሉ አይነትና የቅጣት መጠን ግምት ውስጥ ለምሳሌ የሙስና ወንጀል፤የቅጣቱን ጣራ መሰረት በማድረግ ለምሳሌ የሞት ቅጣት፤የተጎጅዎችን ዓይነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለምሳሌ ሴቶች እና ህፃናት እያልን ብንመለከት ዋስትና የሚያስከለክሉ ናቸው፤፤

# ዋስትና ለመፍቀድም ሆነ ለመከልከል የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

የዋስትና መብት ማግኘት በመርህ ደረጃ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችም ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 19/2/ የተረጋገጠ መብት ነው። ሆኖም ለጠቅላላው ማህበረሰብ ጥቅም ሲባል ይህ መብት ሁሌም ፍፁም ግን አይደለም። ይህ መብት ሲከለከል ቅድሚያ ግምት ውስጥ ከሚገቡ ሁኔታዎች መካከል የኢትዮጵያ የፍትህ ፖሊሲ ተከታዮቹን ቅድመ ሁኔታዎች ይዘረዝራል። እነዚህም የወንጀሉ ጉዳይ ከባድነት፣የተጠርጣሪው ያለፈ የወንጀል ሪከርድ እና

---

[36] https://www.courts.state.nh.us/bail.commissioners
[37]ጸጋየ ወርቃየሁ ስለ ዋስተውና ከሰጡት ስልጠና የተወሰደ
[38] አዋጅ ቁጥር 235/1993 መጀመሪያ የተቋቋመ ሲሆን ከህገ- መንግስቱ ጋር እንዲጣጣም ተብሎ አዋጅ ቁጥር 433/1997 ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡ ኋላም 883/2007 በድጋሜ ተሻሽሏል፡፡
[39] Kalali Kiros, The bail justice in Ethiopia challenges of its administration.page 81
‹‹The new criminal cod of the FDRE contains atotal of 865 provitions. Among them the first 237 provitions deals with general principles while the remaining provitions deals with the spesfic as well as with some other general principies applicable to certain offences.over all around 400 types of offences are recognized under the cod. Among them around 100 types of offences are punishable with not lss than fifteen years imprisment in persont 25% of the cod.››

የግል ጸባይ፣በዋስትና ጥያቄው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በህዝብ ጥቅም ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ ተጠርጣሪው በዋስትና ቢለቀቅ በተፈለገ ጊዜ ፍ/ቤት ተመልሶ ሊቀርብ የሚችል መሆን፣ሌላ ወንጀል ሊፈፅም የማይችል ስለመሆኑ ወይም ምስክሮችን በማስፈራራትና ማስረጃን በማጥፋት በፍትህ አሰጣጡ ላይ እክል ሊፈጥር የሚችል መሆን አለመሆን የሚሉት ሲሆኑ እነዚህን በወንጀለኛ መወሰኛ ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 67 ስር ያሉት ናቸው፡፡[40] ረቂቁ የወ/መ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 139 ዋስትና በፍ/ቤት የሚከለከሉበት ሁኔታ አስቀምጧል፡፡[41] ሆኖም የተከሳሽን ያለፈ ቅጣት ውሳኔን በማያያዝ የዋስትናን ጥያቄ አለመቀበል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 13055 ቅፅ 23 አግባብነት የለውም ብሏል፡፡

## ዋስትና መቼ ቀሪ ይሆናል?

ረቂቁ የወ/መ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 148 እንደተገለፀው ዋስትና በሚከተሉት ጉዳዮች ቀሪ ይሆናል፡፡ ከእነርሱም መካከል ተከታዮቹን ዘርዝሮ እናገኘዋለን፡፡

- ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በነፃ ከተለቀቀ ወይም የተፈረደበት እንደሆነ ፍ/ቤቱ የዋስትናውን ግዴታ ገቢ የማይሆኑበትን ምክንያት ካረጋገጠ ዋስትናው ቀሪ እንዲሆን ያዛል፡፡
- የዋስትና ግዴታውን የፈረመው ዋስ የሞተ እንደሆነ ተጠረውጣሪው ወይም ተከሳሹ ሌላ ዋስ ይጠራል፡፡
- ዋሱ በህግ ችሎታ ያጣ እንደሆነ የዋስትና ግዴታው ቀሪ ይሆናል በሚል ተዘርዝረዋል፡፡

# የዋስትና መብት አለመከበር የሚያስከትለው ጉዳቶች

- ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከቤተሰቦቹ፣ከጓድኞቹ ያለው ጠቅላላ ግንኙነት እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡
- ከስራ ሊባረርና ስራ አጥ ሊሆን ይችላል፡፡
- ቤተሰቦቹን መርዳት ስለሚያቆም ቤተሰቦቹ ለችግር ይጋለጣሉ፡፡
- ተጠርጣሪው መልሱን በአግባቡ እንዳያዘጋጅ ያደርገዋል፡፡
- ተጠርጣሪው ከጠበቃው ጋር እንደልቡ እንዳይገናኝ ያደርገዋል፡፡
- እንደኛ ሀገር ሁኔታ የማረሚያ ቤት እጥረት ወይም የተሸለ ማረሚያ ቤት ባለመኖሩ ለረሀብ፣ለችግር፣ለጤና መታወክ ምክንያት ይሆናል፡፡[42] የተያዘን ሰው በዋስትና መልቀቅ በማረሚያ ቤት ያለውን የእስረኞች መጨናነቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡
- ለማህበራዊ መገለል ይጋለጣሉ፣ለተላላፊ በሽታዎች ማለትም ለሱስ፣ለትቢ፣ለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ተጠቂ ይሆናሉ ፡፡
- የተጠርጣሪዎችና የታራሚዎች እስር ቤት አንድ ላይ በመሆናቸው ተጠርጣሪዎች የማያውቁትን ወንጀል ሊማሩ ይችላሉ፡፡[43]
- ለመንግስት በጀትም ቢሆን ብዙ ተጠርጣሪዎች የዋስትና መብት የሚነፈጉ ከሆነ የሚጎዳ መሆኑ ልብ ይሏል፡፡

---

[40] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ-2003

[41] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ስ/ስ/እና የማስረጃ ህግ ረቂቅ

[42] Simeneh Kirose Assefa, Criminal Procedure law,principles, Rules and Practices page 233‹‹ the budget for food is 2 birr aday for each meal, medical car is scarce, the prisons conditions are:realy intolerable›› በማለት ጥናቱ የእስር ቤቱን አስቸጋሪነት አመላክቶ ነበር፡፡

[43] Kalali Kiros, The bail justice in Ethiopia challenges of its administration.page 88

## የዋስትና መብት መፍቀድ ጥቅሞች

ተከሳሽ ወይም ተጠርጣሪው የመከላከያ አቤቱታውን እንዲያዘጋጅ እና ማስረጃዎቹን እንዲያሰባስብ በቂ ጊዜና አመች ሁኔታን ይፈጥርለታል፡፡ ለምሳሌ ምስክሮቹን ለይቶ የሚያውቃቸው ራሱ ተከሳሹ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

- ከጠበቃው ጋር እንደልቡ እንዲነጋገር ያስችለዋል፡፡ ፍትህ ለመጠበቅ ካስፈለገ አንድ ተከሳሽ መከላከያ መልሱንና ማስረጃውን በደንብ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ከላይ የዋስትና መብት አለመፍቀድ የሚያስከትሉት ችግሮች የተባሉት በጠቅላላው እንዲቀሩ ያደርጋል፡፡ እንደ ሀገርም የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

## የዋስትና መብት በኢትዮጵያ ህግ-መንግስት

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ዋስትና መሰረታዊ መብት ነው፡፡ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 19/6/ መሰረት በዋስትና መፈታት መብት ሲሆን በልዩ ሁኔታ ዋስትና የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ደንግጓል፡፡ ይህም ከዓለም አቀፋዊ ቃል ኪዳን ሰነዶችም ጋር የሚጣጣም ነው፡፡[44] ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች ዋስትና በሁለት ዓይነት ሁኔታዎች ሊከለከሉ እንደሚችሉ ያሳያሉ፡፡ አንደኛው በህግ አውጭው ዋስትና የሚያስከለክሉ ድንጋጌዎች አስቀድሞ የሚከለከልበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህም የህገ-መንግስት ጉባኤው በእነ ጥላሁን አባይ ጉዳይ በሰጠው አስተያየት ህገ-መንግስታዊነቱን አስቀድሞ በህግ መከልከል ይቻላል ብሏል፡፡[45] ሁለተኛው በዳኞች በወንጀል መወሰኛ ስ/ስ/ህግ ቁጥር አንቀፅ 67 ስር ከተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች አንደኛው ሁኔታ ሲሟላ አስቀድሞ በዋስትና የማያስከለክል ድንጋጌም ቢሆን ዋስትና ይከለከላል፡፡ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 19/6/ ዋስትና የሚፈቅደውም የሚከለክለውም ፍ/ቤቶች እንጅ ህግ አውጭው አስቀድሞ መሆን የለበትም የሚል ክርክር ይነሳል፡፡ የተሸሻለው የፀረ ሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 882 አንቀጽ 3 እንደተገለጸው ከ10 ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ የተያዘ ሰው በዚህ ሁኔታ በመገኘቱ ብቻ ዋስትና ይከለከላል፡፡[46] ዋስትና በህግ አውጭው አስቀድሞ መከልከል የለበትም የሚሉትም ሆነ ዋስትና መከልከልን ይፈቅዳል የሚሉት ወገኖች እንደምክኒያት የሚያነሱት የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 19(4)ን ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡ ሆኖም እንደ እኛ ሀገር ባለ የአስፈፃሚ አካላት ሁሉንም ጠቅልሎ በያዘበት ሁኔታ በህግ አስቀድሞ ዋስትና መከልከሉ የዜጎችን መብት በእጅጉ አደጋ የሚጠል ነው፡፡ ዋስትናን ለመከልከል በልዩ ሁኔታ በመሆኑ ለመከልከል የሚዎጡ ህጎችም በዝርዝር እና በጠባቡ መንገድ መሆን አለበት፡፡

## በዋትና መብት መከበር ላይ ፖሊስ ይግባኝ ማለት ይችላል ወይ?

በፍርድ ቤት የተያዘ ሰው የቀረበውን በዋስ ልለቀቅ አቤቱታ ካልተቀበለው በወ/መ/ስ/ስ ህግ አንቀፅ 75 ላይ በተመለከተው መሰረት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው የዋስትና መብቱን ከተከለከለ በስነ-ስርዓት ህጉ ለተጠርጣሪው የይግባኝ መብት በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን በተቃራኒው ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ፍ/ቤት ቢወስን ፖሊስ ይግባኝ እንዲያቀርብ የስነ ስርዓት

---

[44] አማራ ክልል የፍትህ ባለሙያወች ማሠልጠኛ እና የህግ ምርምር እኒስቲትውት የህግ መፅሄት -ቅፅ 5 - ገፅ 78
[45] Ibid-78
[46] https://www.abyssinianlaw.com/blog/20/ የተወሰደበት 22 Jun,2023

ህጉ ይፈቅደውለታል ወይ የሚለው ቀጣዩ ጥያቄ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ፖሊስ ይግባኝ እያልኩ ስለሆነ ተጠርጣሪውን አለቅም እያለ በተለይ በፌደራል ፍ/ቤቶች ተደጋግሞ እየሰማን ነው፡፡ የወንጀለኛ መወሰኛ ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 59/2/ በግልፅ እንደሚያሳየው ፖሊስ ምርመራውን ካላጠናቀቀ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ሊጠይቅ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጅ ይህንን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ሳይቀበል የተያዘውን ሰው ዋስትና ጠብቆ በዋስትና እንዲለቀቅ ውሳኔ ከሰጠ ፖሊስ ይግባኝ የማለት መብትን ድንጋጌው አላጎናፀፈውም፡፡ የተሻሻለው የሽብር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀፅ 45 በግልፅ እንደተመለከተው የተከሰሰ ሰው አያያዙ ከህገ-መንግስቱ እና አለም አቀፍ ህጎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ይህ አዋጅ ፖሊስ ይግባኝ ይላል አይልም፡፡ የተሻሻለው የኢ.ብ.ክ.መ ፖሊስ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216 ፖሊስ በተሰጠ የዋስትና ውሳኔ ወይም ብይን ይግባኝ እንደሚል አላካተተም፡፡ ታዲያ ከላይ ያየናቸው ህጎች ፖሊስ ይግባኝ እንደሚል ካላስቀመጡ በየትኛው የህግ መሰረት ነው ፖሊስ ይግባኝ የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ፖሊስ በተደጋጋሚ በሚያቀርባቸው አቤቱታዎች በተለይ የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በህገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን የዋስትና መብት በእጅጉ እያጠበበ የመጣ አሰራር በመሆኑ ፍ/ቤቶች የተየዙ ሰዎችን መብት ለማስከበር ያላቸውን ሚና የሚሸረሽር ተግባር ሲሆን የተጠርጣሪዎችን አላስፈላጊ እንግልትን የሚፈጥር ነው፡፡[47] ፖሊስ ይግባኝ ለማለትም በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አንቀፅ 743 የሚጠቀሙ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ግን በተከበረ የዋስትና መብት አዲስ ነገር ሲገኝ የተሰጠውን ውሳኔ ለማሻሻል የተቀመጠ የህግ ድንጋጌ ነው፡፡ ወዲያውኑ በተወሰነ ጉዳይ ላይ አዲስ ነገር ባልመጣበት ሁኔታ አዲስ ነገር አለኝ ማለትም አይቻልም፡፡ ሌላው በዚህ ድንጋጌ የተካተተው የዋስትና ውሳኔው በሰጠው ፍ/ቤት ሲሆን ይግባኝ ማለትን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ፖሊስ ይግባኝ እላለሁ በሚል የህግ መሰረት በሌለው ምክንያት የዋስትና መብት የተፈቀደላቸው ዜጎችን መከልከልስ ይችላል ወይ? ይግባኝ የማለት መብት ለለው ካልንስ የዋስትና መብታቸው የተከበረላቸው ተጠርጣሪዎችን ፈቶ ይግባኝ ማለትስ አይገባውም ወይ? መፍትሄው በመቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2006 አንቀፅ 6/4/ መሰረት በግልፅ እንደተደነገገው የፍ/ቤቶችን ትዕዛዝ አክብሮ መፈጸም ብቻ ነው፡፡

## አካል ነፃ መውጣት( Habeas Corpus)

የተያዙ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍ/ቤት ማቅረብ እንዳለባቸው ህጉ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በጊዜው ፖሊስ ፍ/ቤት የተያዙ ሰዎችን ይዞ ሳይቀርብ የተያዙ ሰዎች ዕጣ ፈንታ /ተጠርጣሪዎችን የያዘ አንድ የህግ አስከባሪ/ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ፍ/ቤት አቅርቦ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልገው ከሆነ ጊዜ ቀጠሮ መጠየቅ አልያም ካጠናቀቀ በፖሊስ ዋስ ወይም በፍ/ቤት እንዲለቀቁ ማድረግ አለበት፡፡ ይህንን ካላደረገ የአካል ነፃ የመሆን አቤቱታቸውን የማቅረብ መብት አላቸው፡፡[48]

---

[47] https://www.abyssinianlaw.com/blog/the -legal-implication-of-an-appeal-submitted-by-the- police-on-the-enforcement-of-the-right-to-bail-

[48] https://www.ezega.com/News/# የተወሰደበት ቀን may 23/2023

## አካል ነፃ የመውጣት/Habeas Corpus/ ትርጉም

ለዚህ ክስ ወይም አቤቱታ መነሻ የሚሆነው ከላይ እንደተመለከትነው ህገ-ወጥ የፖሊስ እስራትን ለመቃወም ሲሆን የቃሉ ትርጉም መነሻው የላቲን ቋንቋ ነው፡፡ ትርጉሙም "You Have The Body" የሚል ነው፡፡ አገባባዊ ፍቹም "ፖሊስ ሆይ … ግለሰቡን ይዘኸዋል እስራቱ በህግ አግባብ ስለመሆኑ ግን ወደ ፍ/ቤት አምጣቀው" የሚል መልዕክት አለው፡፡[49] መነሻውን ጸሀፍት ወደ 17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚወስዱት ሲሆን መብቱ የተጀመረው እንዳሁኑ ከህገ-ወጥ የፖሊስ እስራት ለመፍታት ሳይሆን በጊዜው የነበረውን የባሪያዎች፣የስደተኞች እና የጦር ምርኮኞችን ህገ-ወጥ እስር ህጋዊነቱን ለማረጋገጥ ተብሎ ነበር፡፡[50] በሀገረ አሜሪካም በእነ አብርሀም ሊንከን ዘመን አገልግሎት የዋለ ሲሆን በ2ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ለምርኮኞች ተብሎ አገልግሎት መዋሉን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡[51] ይህ ለምርኮኞች፣ለስደተኞች እና ለባሪያዎች/Slaves/ መብት ተብሎ የተጀመረው የሰብዓዊ መብት ኂላ የሰው ልጅን ክብርና ነፃነት እየተጋፋ የመጣውን ህገ-ወጥ መንግስታዊ እስር/Unlawful/Unjustified Detention/ መከላከያ መንገድ ሆኑ መጥቷል፡፡ ይህ መብት በእኛም ህጎች የተካተተ ሲሆን የማሰር ስልጣን የሌለው አካል ወይም ባለስልጣን ትዕዛዝ የታሰረ ሰው ፖሊስ ከ48 ሰዓት በላይ ለሆነ ጊዜ በማሰር ለፍ/ቤት አላቀረበኝም በሚል ያለአግባብ ታሰርኩ በማለት የሚቀርብ አቤረቱታ ሲሆን ፍ/ቤቱም ማመልከቻው እንደደረሰው ወዲያውኑ ፖሊስ ተጠርጣሪውን ይዞ እንዲቀርብ ወይም እንዲፈታ የሚያዝበት ስርዓት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም እውቅና ከተሰጣቸው ከሰብአዊ መብቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ አንቀፅ 17 በግልፅ እንደሚያሳየው ማንም ሰው ከህግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሊያዝ እንዲሁም ክስ ሳይቀርብበትና ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም ብሏል፡፡ ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ስምምነት ሰነዶችም ቢሆን እውቅና ሰጥቶታል፡፡ ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በፍትሐብሔር ዳኝነት ሲሆን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር አንቀፅ 15/2/ቀ እና ከ177-197 ባሉት ድንጋጌዎች የሚመራ ነው፡፡ ይህ ክርክር በፍ/ስ/ስ/ህጉ በተለየ የሙግት ስርዓት የተቀመጠ ሲሆን ከመደበኛው የፍትሐብሔር ክርክር የሚለይ ነው፡፡ የሚለይባቸው መንገዶችም፡-

1. **አቤቱታውን ለማቅረብ የግድ ራሱ አመልካች ላይሆን ይችላል፡፡**

የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 33 መሰረት ከሳሽ የመሆን ችሎታ ተቀምጧል፡፡ ይህም ከሳሹ ክስ በአቀረበበት ሰው ላይ የሚጠይቀውን መብት የማሳየት ግዴታ አለበት ማለት ነው፡፡ በተከሳሹ ላይ የሚጠይቀው መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው ይገባል፡፡ በአካል ነፃ መሆን በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የግድ መብቱ በተገፋበት ሰው ወይም በህጋዊ ወኪሉ ብቻ የሚቀርብ አይደለም፡፡ በቃለ መሀላ ማረጋገጥ የሚችል ማንኛውም ሰው መብቱ በተገፋበት ሰው ፋንታ የተያዘው ሰው ወኪል ባይሆንም እንኳ ክሱን ወይም አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ይህም ማለት በማንኛውም ሰው አቤቱታው ፍ/ቤት መቅረብ እንደሚቻል ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን 177/3/ እን አንቀጽ 33/1/ ጣምራ ንባብ እንደምንረዳው አካለ መጠን የደረሰ መሆን፣በፍርድ ያልተከለከለ መሆንና መብቱ የተፋበት ሰው በራሱ አቤቱታውን ማቅረብ እንደማይችል በቃለ መሀላ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህም በቀጥታ መብቱ የተጎዳበት ሰው ባይሆንም እንኳ ከላይ የተገለፁትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ ማንኛውም ሰው ማቅረብ ይችላል፡፡

---

[49] ibid

[50] Amada L. Tyler-Habeas Corpus-Avery Short Introduction-Oxford Page 130

[51] https://www.ezega.com/News/# የተወሰደበት ቀን may 23/2023

## 2. አቤቱታ ለማቅረብ የግድ ውክልና ወይም ሞግዚት አለማስፈለጉ

የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 57 እንደሚያሳየን ሰው በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በአንቀፅ 58 መሰረት ባለሙያ ያልሆኑ ቤተሰቦች በአንቀፅ 63 መሰረት ባለሙያ የሆነ ጠበቃ ተወክሎ እንደሚከራከር ተቀምጧል፡፡ የአካል ነፃነት አቤቱታን ለማቅረብ ግን አቤቱታ አቅራቢው የግድ መብቱ የተጎዳበት ሰው ቤተሰብ አልያም የሙያ ፈቃድ ባይኖረውም ከላይ የተቀመጡትን ቅድመ ሆኔታዎች ካሟላ አቤቱታውን ማንኛውም ሰው ማቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታው ሲቀርብ በራሱ ስም ነው ወይስ መብቱ በተጎዳበት ሰው የሚል ጥያቄ የሚነሳ ሲሆን በአንቀፅ 177/3/ መሰረት መብቱ የገፋበት ሰው በራሱ ሊያቀርብ ባልቻለ ጊዜ ስለሚል በተያዘው ሰው ስም ቢሆን የህግ አውጭውን ሀሳብ የሚያሳካ ይመስላል፡፡

## 3. ፍ/ቤት በአካል የግድ መቅረብ አለማስፈለጉ፡

በመደበኛው የሙግት ስርዓት አንድ ክስ ያቀረበ ሰው እርሱ ካልሆነ ወኪሉ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለባቸው ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 65/1/ ድንጋጌ የምንረዳው ነው፡፡ ሆኖም በልዩ ሁኔታ ፍ/ቤት መቅረብ እንደሚያስፈልግ ህጉ በልዩነት አስቀምጧል፡፡ በአካል ነፃ የመሆን አቤቱታ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ በ178/1/ መሰረት በተከሳሽነት የተጠራው አካል ፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚገባ ያስቀመጠ ሲሆን ከሳሽና ተከሳሽ ማለትም አሳሪና ታሳሪ የግድ ፍ/ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡ ይህም ከመደበኛው የሙግት ክርክር የተለየ መሆኑ ነው፡፡ ምንክንያቱም አንቀፅ 69፣73፣74 ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ክርክር ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የግድ መቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡ በሌላ በኩል የአካል ነፃ የመሆን አቤቱታ ላይ የግድ ሁለቱም እንዲቀርቡ ህጉ የተቀረፀው አላግባብ የታሰረ ከሆነ ያለተጨማሪ ትዕዛዝ ከዕስር እንዲፈታ ለማድረግ የታሰበ ነው፡፡ አሳሪው ባይቀርብ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ከተነሳ በንዑስ ቁጥር 2 መሰረት ፍ/ቤቱ ምስክሮቹን ሰምቶ ሊወስን እንደሚገባ ተቀምጧል፡፡ አሳሪው ቀርቦ አላሰርኩም በማለት ቢክድስ ለሚለውም ጥያቄ ከተነሳም ይህንን በተመለከተም ስለማሰር አለማሰሩ ምስክሮቹን ሰምቶ መወሰን ይገባል፡፡

## 4. የአፈፃፀም ክስ የለውም

የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 371 እንደተደነገገው አንድ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ የፍርድ ባለዕዳው ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ የአፈፃፀም መዝገብ ይከፈታል፡፡ በአካል ነፃ የመሆን አቤቱታ ላይ ግን በተቃራኒው የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 179/2/ መሰረት ፍ/ቤቱ እስሩን አረጋግጦ ህገ-ወጥ መሆኑን ከደረሰበት ከእስር እንዲለቀቅ ይወስናል፡፡ ይህም የሚያሳየን አቤቱታው የሚፈፀመው ሲቀርብ መሆኑ ነው፡፡

## 5. በፍ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 205 መሰረት በቃለ-መሀላ ተረጋግጦ የሚቀርብ መሆኑ

በመደበኛው የሙግት ሒደት መሰረት በአንቀፅ 92 መሰረት በክሱ ላይ የተጠቀሰው ፍሬ ነገር እውነት ስለመሆኑ ያረጋግጣል እንጅ በ205 መሰረት በቃለ መሀላ አይረጋገጥም፡፡ የአካል ነፃ መሆን አቤቱታ ግን እውነት ስለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ተገቢው ቃለ-መሀላ ተፈፅሞበት

በአንቀፅ 177/2/ መሰረት የሚቀርብ ነው፡፡[52] ይህም ከመደበኛው የሙግት ስርዓት የተለየ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

# የአካል ነፃ መሆን ስረ-ነገር ስልጣን

የፌደራል ፍ/ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 13/3/ መሰረት በህገ-መንግስቱ ምዕራፍ 3 ላይ የተቀመጡት የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚቀርብ ክርክር ስረ-ነገሩ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ይሁን እንጅ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 230167 በሆነ ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው የህግ ትርጉም የአካል ነፃ የመሆን ስልጣን የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ብሏል፡፡ አዘጋጁም የሰበር ውሳኔ ከተደራሽነት አንፃር መብታቸው ለተጎዱ ሰዎች መብታቸውን በቀላሉ ለማስከበር የሚያስችል ነው ብሎ ያምናል፡፡ እንደ ክልላችን የፍ/ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀፅ 14/3 በግልፅ የወረዳ ፍ/ቤት መሆኑን ያስቀመጠ ቢሆንም የተሻሻለው የአ.ብ.ክ.መ የፍ/ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 ለማን እንደሆነ በግልጽ አላስቀመጠም፡፡ አንቀጽ 16/4/ እና አንቀፅ 20ን ጣምራ ንባብ ስንመለከተው ግን ለወረዳ ፍ/ቤት የሰጠ ይመስላል፡፡

# የተመረጡ የሰበር የዋስትና ውሳኔዎች

የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 132055 በሆነ የአንድን ተከሳሽ ያለፈ ቅጣት ውሳኔን አሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ ወንጀል ሊፈፅም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄን አለመቀበል አግባብነት የለውም ያለ ሲሆን በህግ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር አንድ ተከሳሽ በፍርድ ዳኝነት በግልፅ እስካልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ ሊገለፅ አይገባውም በማለት አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡[53] በመ/ቁጥር 146727 በሆነ መዝገብ የወ/መ/ስ/ስ ቁጥር 75/1/ እና /2/ ተከሳሹ በዋስ ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ ባልተፈቀደ ጊዜ እንጅ የስር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤ ህግ ባቀረበው ይፈግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠው ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ እንዲያቀርለብ ተፈፃሚ የሚሆን አይደለም ብሏል፡፡[54] በሌላ በኩልም በመ/ቁጥር 110969 በሆነ ደግሞ ከሳሽ ወገን ዋስትና በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የስነ-ስርዓትስ ህጉ በተለየ ሁኔታ ያካተተው ድንጋጌ ባይኖርም በአንቀፅ 75/1/ ድንጋጌ አንፃር ዋስትና በመፍቀድ በሚሰጥ ትዕዛዝ ዓቃቤ-ህግ ይግባኝ ከማለት የሚከለክላቸው አይደለም ብሏል፡፡[55] በመ/ቁጥር 131863 ላይም ዋስትና በሚያስከለክል ወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም በሚል ፍ/ቤቱ የዋስትና መብቱን ሊነፍግ የሚገባው በዘፈቀደ ሳይሆን ዓቃቤ ህግ ተከሳሹ ቀጠሮውን አክብሮ ሊመጣና የዋስትናውን ግዴታ ሊያከብር አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ሊደርስባቸው የሚችሉ በቂ ምክንያቶችና መረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ ከዓመታት በፊት ያስመዘገበውና አሁን ያስመዘገበው መታወቂያ ላይ አድራሻ ልዩነት ስላለ ቋሚ አድራሻ የለውም በማለት ዋስትና መከልከል አይገባም ብሏል፡፡ [56] በመ/ቁጥር

---

[52] https://www.abyssinianlaw.com/blog/ Habeas- Corpus-in-civil-suits-in-Ethiopia May 30/2023
[53] ቅፅ 23
[54] ቅፅ 22
[55] ቅፅ 18
[56] ቅፅ 20

31734 በሆነ ተከሳሽ ከአንድ በላይ ፓስፖርትና የበርካታ ሀገሮች መግቢያ ቪዛ ያለው መሆኑ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን ግምት ለመውሰድ በቂ መንደርደሪያ ቢሆንም እንኳ ከሀገር የማይወጣበትን/ፓስፖርቱ በፍ/ቤት እንዲቆይ ማድረግ/ ሁኔታ በመፍጠር የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል።[57] በ/ቁጥር 34077 በሆነ ተከሳሽ የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ተፈፀመ የተባለበት ጊዜ የነበረው የተሻረ የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሰረት የዋስትና መብት የሚከለክል ሆኖ በአዲሱ የወንጀል ህግ ግን የሚፈቅድለት በሆነ ጊዜ በመርህ ደረጃ የተሻረ ህግ ተፈፃሚነት የሌለው ሲሆን በተሻረ ህግ ክስ ማቅረብ ደግሞ ልዩ ሁኔታ ነው።[58] ቅጣቱ የሚጣለው ተከሳሹን በሚጠቅመው በአዲሱ ህግ ነው። የዋስትና ጉዳዩም በዋነኝነት የሚታየው ቅጣትን መሰረት አድርጎ ስለሆነ ክርክሩ በተሻረውና ዋስትና በሚከለክል ድንጋጌ የሚመራ ቢሆንም ክርክሩ እልባት ካገኘ በኋላ በተከሳሹ ላይ የሚጥለው ቅጣት የዋስትና መብትን በሚፈቅደው በአዲሱ ህግ ስለሆነ ለተከሳሹ ዋስትና ሊፈቀድለት ይገባል። በመሆኑም ተከሳሹን የሚጠቅም ከሆነ የዋስትና ጉዳዩም ወደ ኋላ ሄዶ ተግባራዊ ይሆናል።[59] በመ/ቁጥር 73569 በሆነ ተከሳሽ የዋስትና መብት ተፈቅዶለት ብሩን አስይዞ እያለ በሌላ ክስ ተፈርዶበት ማረሚያ ቤት ከገባ በሌላ ክስ ያስያዘውን ዋስትና መጠቀም ስለማይችል የዋስትናው ብር ተመልሶለት ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ነው ብሏል። አያይዞም የዋስትና መብቱን በመተው ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል ፍላጎት ያለው መሆኑን ሲገልፅ ሊነፈግ አይገባውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።[60] በመ/ቁጥር 67874 በሆነ የወ/መ/ስ/ስ ህግ አንቀፅ 67 በጠቅላላው ሲታይ ፍ/ቤቱ ከተለያዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባ ሲሆኑ የድንጋጌው ቅርፅ፣ይዘትና መንፈስ ስንመለከተው የፍ/ቤቶች ስልጣን መሆኑን ያሳያል። የሰበር ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተትን ማረም እንጅ የማስረጃና የሌሎች አካባቢያዊ ነገሮችን ምዘና ጉዳይ ተገቢ መሆን አለመሆንን ማረም ስላልሆነ የስር ፍ/ቤቶች ስልጣን ነው ብሏል።[61] በመ/ቁጥር 35695 በሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3/ እና የወንጀል መወሰኛና ስ/ስ/ህ/ቁጥር 63/1/ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላና የዋስ መብት የማያስፈቅድ ነው።[62] በመ/ቁጥር 68407 በሆነ በወንጀል ህግ ቁጥር 407/2/ ተመለከተውን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው በካንሰር በሽታ መታመማቸው ውጭ ሀገር ሄደው ለመታከም ዋስትና እንዲፈቀድላቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። የወንጀል ህጉ ከ7 ኣመት እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተከሳሽ በህግ ጥላ ስር መዋል ወይም የዋስትና መብት መከልከሉ የተከሳሽን የህክምና የማግኘት መብት ነክቷል አያስብልም። በህግ ጥላ ስር ያለ ሰው የህክምና መብቱ የማይገደብበትና መሰረታዊ መብቱ እንደማንኛውም ዜጋ የሚከበርለት በመሆኑ ዋስትናው ተከለከለ ማለት የህክምና መብቱ ተገደበ ማለት ባለመሆኑ ተከሳሽ ለሚመለተው አካል በማመልከት ህክምናውን ማግኘት ይችላል በማለት አስገዳጅ ውሳኔ ከሰጠባቸው ውሳኔዎች ጥቂቶቹ ናቸው።[63]

---

[57] ቅፅ 7
[58] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5
[59] ቅፅ 7
[60] ቅፅ 13
[61] ቅፅ 13
[62] ቅፅ 9
[63] ቅፅ 12